11ኛ ዓመት ቁጥር 1
11th Year No. 1

ባህር ዳር ጥር 10 ቀን 1998 ዓ/ም
Bahir Dar January 18, 2006

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 6.75
Unit price -----

ማውጫ	Content
አዋጅ ቁጥር 119/1998 ዓ.ም የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት ስነ-ምግባር፣ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሠራር መወሰኛ አዋጅ	Proclamation No. 119/2005 The Revised Proclamation for Defining Ethics, Legislative Procedure, Committee Organization and Operation of the Amhara National Region Council Members.

አዋጅ ቁጥር 119/1998 ዓ.ም

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት ስነ-ምግባር፣ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የክልሉ ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስትና በሕዝቡ የተጣለበትን ኃላፊነት በበለጠ ለመወጣት ይቻለው ዘንድ ከሕገ-መንግስቱ ጋር የተገናዘበና ብቃት ያለው ውስጣዊ አደረጃጀት፣ የተሟላ የአሠራር ስልትና ዝርዝር ሥነ-ሥርዓቶች መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በስራ ላይ ያለውን የቋሚ ኮሚቴዎች አወቃቀርና አሠራር መርምሮ የክልሉን መንግስት አካላት አደረጃጀት ባገናዘበ ሁኔታ እንዲሻሻል ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

Proclamation No. 119/2005

The Revised Proclamation Issued to Define Ethics, Legislative Procedure, Committee Organization and Operation of the Amhara National Region Council Members

WHEREAS, it is found necessary to lay down efficient internal organization, complete operational system and rules of procedures in line with the Constitution with a view to enabling the Regional Council to better discharge the responsibilities entrusted on it by the Revised Constitution of the National Region and the public as well;

WHEREAS, it is found appropriate to examine and thereby amend the existing structure and operation of standing committees of the Regional Council in line with organization of government bodies of the Region;

የምክር ቤቱን አባላት መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም በምክር ቤቱ ውስጥ መቀመጫ ያላቸውን የፖለቲካ ፓርቲ ተጠሪዎች አደረጃጀትና ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና አስመልክቶ በዝርዝር መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHEREAS, it is necessary to particularly stipulate pertaining to rights and duties of members of the Council and organization and role of those party whips which have seats in the Council;

የህዝብ ወኪሎች የሆኑት የምክር ቤቱ አባላት የሚጠበቅባቸው የሥነ-ምግባር ደረጃ ከክልሉ ህገ-መንግስት ድንጋጌዎችና ከፌዴራሉ መንግስት የፓርላማ አሠራር መርሆዎች ጋር የተጣጣመ ሆኖ ዲሞክራሲያዊ ባህሪያትን የሚያጐለብትና አንፃራዊ ተጠያቂነት ያለበት ሆኖ እንዲቀረጽና ለሕዝብ ግልጽ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is necessary to formulate the ethical standard expected from people's deputies in conformity with the provisions of the National Regional Constitution and operational principles of the Federal Parliament and thereby make it public in order to promote democratic attributions and previal accountability thereof;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 49/ንዑስ አንቀጽ 3/1 ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል::

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the powers vested in it under Article 49 sub Article 3/1/, issues the following proclamation.

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የምክር ቤት አባላት ስነ-ምግባር፣ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሠራር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 119/1998 ዓ.ም. " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

Part One
General

1. Short Title

This Proclamation may be cited as " The Revised Council Members Ethics, Definition of Legislative Procedure, Committee Organization and Operation Proclamation No.119/2005."

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. "ሕገ-መንግስት" ማለት ጥቅምት 26 ቀን 1994 ዓ.ም. ተሻሽሎ የወጣው የአማራ ብሄራዊ ክልል ሕገ-መንግስት ነው::
2. "ምክር ቤት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ነው::
3. "ኮሚቴ" ማለት አንድን ጉዳይ ለማከናወን እንደየሁኔታው በም/ቤቱ የሚቋቋም አስተባባሪ፣ ቋሚ፣ ንዑስ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው::

2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this proclamation:

1. "Constitution" means the Revised Constitution of the Amhara National Region issued on November 5,2001.
2. "Council" means the Amhara National Regional Council.
3. "Committee" means coordinating, standing, Sub-or Ad hoc committee established, as the case may be, by the Council to undertake the function of the Council.

4. "ቋሚ ኮሚቴ" ማለት በህግ ተወስኖ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር ዙሪያ በቋሚነት የሚሰራ ሆኖ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/4 መሰረት ምክር ቤቱ የሚያቋቁመው ቋሚ ኮሚቴ ነው::

4. "Standing Committee" means the standing committee established pursuant to Article 49 sub-Articles 3(4) of the Constitution to act perpetually within its legally provided jurisdiction.

5. "ጊዜያዊ ኮሚቴ" ማለት አስቸኳይ ሁኔታ ሲፈጠር፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና ተግባሩ በሌሎች ኮሚቴዎች በቀጥታ ሊከናወን የማይችል ነው ብሎ ሲያምን ምክር ቤቱ የሚያቋቁመው ኮሚቴ ነው::

5. " Ad-Hoc Committee" means a committee to be established by the Council where there is urgent situation and deems necessary, and when the Council believes such function cannot be specifically undertaken by other committees.

6. "ንዑስ ኮሚቴ" ማለት ማንኛውም የም/ቤቱ ኮሚቴ ለሥራው ቅልጥፍና እንዲያግዘው ከራሱ አባላት መካከል መርጦ የሚያቋቁመው ኮሚቴ ነው::

6. " Sub Committee" means a committee which any committee of the Council establishes electing from among its own members for the expedition of its activities.

7. "አስተባባሪ ኮሚቴ" ማለት የምክር ቤቱን አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ የቋሚ ኮሚቴዎችን ሰብሣቢዎችንና ፀሃፊዎችን የያዘ አካል ነው::

7. "Coordinating Committee" means a body consisting of the speaker and the deputy Speaker of the Council, chairpersons and secretariats of the standing committees.

8. "አስረጅ" ማለት እንደ ሁኔታው በምክር ቤቱም ሆነ በኮሚቴዎች ረቂቅ ህግን ወይም እንዲብራራ የተፈለገን አንድ ጉዳይ እንዲያብራራ የሚጠራ ሰው ወይም አካል ነው::

8. "Resource Person" means a person or a body invited by the Council or committees to expouad his/her views on a draft law or on required issues.

9. "የመጀመሪያ ንባብ" ማለት ማናቸውም የህግ ረቂቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአፈ-ጉባኤው ቀርቦ ከአስተባባሪ ኮሚቴው አባላት ጋር በመሆን በሰነዱ መሰረታዊ ይዘት ላይ አጠቃላይ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ለዝርዝር እይታ ወደ ሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ የመምራት ሂደት ነው::

9. " First Reading" means the process of reading and general discussion held on fundamental concepts of a draft law by members of the coordinating committee having been submitted to the Speaker before it gets referred to the pertinent standing committee.

10. "ሁለተኛ ንባብ" ማለት ከመጀመሪያ ንባብ በኋላ ማናቸውም የህግ ረቂቅ በአስተባባሪ ኮሚቴው አማካኝነት ለዝርዝር እይታና ምርመራ ወደሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ከተመራ በኋላ ቋሚ ኮሚቴው ለምክር ቤቱ የሚያቀርበው ሪፖርትና የውሣኔ ሃሣብ ሲሆን በቀረበው የኮሚቴው ሰነድ ላይ የሚደረግን ውይይት ይጨምራል::

10. "Second Reading" means the discussion on the recommendation and suggestion of the concerned standing committee, to which the draft law was referred for further inspection by the coordinating committee subsequent to the first reading and thereby presented to the Council.

11. "ሶስተኛ ንባብ" ማለት ከሁለተኛ ንባብ በኋላ በስፋትና በጥልቀት እንዲታይ ምክር ቤቱ ለቋሚ ኮሚቴ የመራው ረቂቅ ሕግ እንደገና ወደ ምክር ቤቱ ተመልሶ የሚደረገው የውይይት ሂደት ነው::

12. "የቴክኒክ እርማት" ማለት ማንኛውም የቋንቋና መሰል ግደፈቶችማስተካከያ ሲሆን በማናቸውም ረገድ የህጉን ይዘት የማይለውጥ ማሻሻያ ነው::

13. "መንግስታዊ አካላት" ማለት ምክር ቤቱ ወይም ኮሚቴዎቹ በቀጥታ የሚከታተሏቸውና የሚቆጣጠሯቸው ሆነው መንግስት በጀት የሚመድብላቸው ተቋማት ናቸው::

14. "የመንግስት ተጠሪዎች" ማለት በምክር ቤቱ ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ ወይም ያገኙ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ጣምራ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክር ቤቱ ውስጥ የድጅታቸውን ወይም የድርጅቶቻቸውን ሥራዎች እንዲያስተባብሩ የሚወክላቸው ወይም የሚወክሏቸውና የምክር ቤት አባል የሆኑ አባሎቻቸው ናቸው::

15. "የዋና ተቃዋሚ ፖርቲ ተጠሪዎች" ማለት የክልሉን መንግስት ከመሰረተው ወይም ከመሰረቱት የፖለቲካ ፖርቲ ወይም ጣምራ የፖለቲካ ፖርቲዎች በመቀጠል ብዙ መቀመጫዎችን ያገኘ የፖለቲካ ፖርቲ ስራዎችን በምክር ቤቱ ውስጥ እንዲያስተባብሩ የሚወክላቸውና የምክር ቤት አባል የሆኑ የፖርቲው አባሎች ናቸው::

16. "የሁለተኛ ተቃዋሚ ፖርቲ ተጠሪዎች" ማለት ከዋናው ተቃዋሚ ፖርቲ ቀጥሎ ብዙ መቀመጫዎችን ያገኘ የፖለቲካ ፖርቲ የፖርቲውን ሥራዎች በምክር ቤቱ ውስጥ እንዲያስተባብሩ የሚወክላቸውና የምክር ቤት አባል የሆኑ የፖርቲ አባሎች ናቸው::

17. "የመንግስት ረቂቅ ህግ" ማለት በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ውሣኔ ተደግፎ ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ረቂቅ ህግ ነው::

11. " Third Reading" means the discussion of the Council members on the returned draft legislation, which was earlier referred to the standing committee(s) for further re-examination subsequent to the second reading.

12. "Technical Correction" means rectification of language and language like errors that in no way modifies the substance of the given law.

13. "Government bodies" means bodies that are directly supervised and investigated by the Council or committees, and to whom the government allocates budget.

14. "Government whips" means members of the Council representing the political party or coalition of political parties that have won majority seats in the Council to coordinate activities of their party (parties).

15. "Whips of Main Opposition Party" means members of the Council representing the political party who, has majority seats next to the political party or coalition of political parties which have formed the Regional Government to coordinate activities of their party in the Council.

16. "Whips of Second Opposition Party" means members of the Council representing the political party, who has majority seats next to the main opposition party, to coordinate activities of their party in the council.

17. "Government Draft Law" means a draft law supported by decision of the Council of the Regional Government and presented to the Council.

18. "ብዙሃን ማህበራት" ማለት በእደሜ በጾታና በሙያ የተደራጁ አባላትን የያዙና ህጋዊ እውቅና የተሰጣቸው ማህበራት ናቸው።

18. "Civic Association" means associations legally reconized and consisting of members organized in age, sex and profession.

ክፍል ሁለት

ስለም/ቤቱ አደረጃጀት ዋና ዋና ተግባራትና የአሠራር ሥርዓት

Part Two

The Structure, Major Duties and Working Procedure of the Council

3. የምክር ቤቱ አጠቃላይ አደረጃጀት

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የምክር ቤቱ አደረጃጀት እንደሚከተለው ይሆናል፦

   ሀ. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ

   ለ. የአፈ-ጉባኤው ጽ/ቤት

   ሐ. የምክር ቤቱ ልዩልዩ ኮሚቴዎች

   መ. የመንግስትና የፖርቲ ተጠሪዎች /Whips/

   ሠ. የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተዘረዘሩት አካላት ሥልጣንና ተግባር በዚሁ አዋጅ የተደነገገ ሲሆን የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባራት ግን በሚቋቋሚያ አዋጁ መሰረት የተወሰነ ስለሆነ በዚህ አዋጅ አልተመለከተም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች አካላትን ሊያቋቁም ይችላል።

3. General Structure of the Council

1. The structure of the Council, pursuant to this proclamation, shall be the following:

   a. The General assembly of the Council

   b. The office of the Speaker

   c. Various committees of the Council

   d. Whips of political parties that have seats in the Council.

   e. The Secretariat of the Councii.

2. The powers and duties of bodies specified under sub-Article 1 of this Article shall be provided in this proclamation. However, the powers and duties of the secretariat of the Council are not enumerated by this proclamation, as they are covered by the proclamation for its establishment.

3. Nothwithstanding the provision of sub-Article 1 of this Article, the Regional Council may establish other bodies when it deems necessary.

4. የምክር ቤቱ አጠቃላይ ተግባራት

ምክር ቤቱ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 49 ከተሰጠው ስልጣን የሚመነጩ ሆነው የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. ልዩ ልዩ ህጐችንና ደንቦችን ማውጣት፤

4. Major Duties of the Council

The Council, deriving its powers from Article 49 of the Constitution, shall have the following major duties and responsibilities:

1. Enact various laws;

2. ርዕሰ መስተዳድሩንና ሌሎች የክልሉን መንግስታዊ አካላት ለጥያቄ የመጥራትና የሕግ አስፈፃሚውን አካል አሠራር መመርመር፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፤

3. የተለያዩ ሹመቶችን ማጽደቅ ወይም እንደአግባብነቱ መስጠት፤

4. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ኮሚቴዎችን ማደራጀትና ሪፖርታቸውን ማዳመጥ መመሪያዎችን መስጠት ወይም ውሣኔዎችን ማሣለፍ።

5. ስለአፈ-ጉባኤውና ምክትል አፈ-ጉባኤው አመራረጥ

1. በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/4/ መሰረት ምክር ቤቱን የሚመሩ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ በምክር ቤቱ ይመረጣሉ።

2. አፈ-ጉባኤውን ለማስመረጥ በመስራች ጉባኤው መክፈቻ ላይ በሚገኝ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ተወካይ አማካኝነት 5 አባላትን የያዘ አስመራጭ ኮሚቴ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ተመርጦ ይሰየማል።

3. ለአፈ-ጉባኤነት እጩ ሆነው የሚቀርቡት ከ2 የማይበልጡ የምክር ቤት አባላት ይሆናሉ። እነርሱም የምክር ቤቱን ተሰብሣቢ አባላት 1/3 የድምፅ ድጋፍ ያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል።

4. የቀረቡት እጩዎች ከአንድ በላይ በሆኑ ጊዜ አፈ-ጉባኤው የሚመረጠው እጅ በማውጣት ሲሆን አብላጫ ድምፅ ያገኘው የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ይሆናል።

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቢኖርም አንድ ተወዳዳሪ ብቻ በእጩነት በቀረበ ጊዜምክር ቤቱ በቀጥታ ድጋፍ /አክላሜሽን/ አፈ-ጉባኤውን ይመርጣል።

6. አፈ-ጉባኤውን አስመልክቶ ከዚህ በላይ የተፃፉት ድንጋጌዎች ለምክትል አፈ-ጉባኤውም አመራረጥ በተመሣሣይ ይሰራባቸዋል።

2. Call Head of the Government and other government bodies of the Region for questioning; examine the operations of the Exectuive Body and take appropriate measures when it deems necessary;

3. Approve the appointment of government officals and give appointments as deemed appropriate;

4. Organize committees necessary for its functions, hear their reports; and give guidelines and pass diceisions thereon.

5. Nomination of the Speaker and the Deputy speaker

1. The Council, in accordance with Article 49 sub-Article 3 /4/ of the Constitution, shall elect a Speaker and Deputy Speaker of the Council.

2. An election committee comprising five candidates shall be elected from among Council members upon presence of a representative from the National Electoral Board during the inaugural meeting to get the Speaker elected from council members.

3. Candidates presented to be a Speaker shall not be more than two Council members. The candidates shall be supported by one-thirds vote of the Council members present in a meeting.

4. When there is more than one candidate, the election of a Speaker shall be by raising hands, and then a candidate who has got majority vote of the council shall be the Speaker.

5. Notwithstanding the provision of sub-Article 4 of this Article, the Council shall elect the Speaker by acclamation when only one candidate is forwarded.

6. Provisions stated hereof concerning the election of the Speaker shall also apply for election of the Deputy Speaker.

6. የአፈ-ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

አፈ-ጉባኤው በህገ-መንግስቱና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የም/ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፣ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመቀናጀት ዕለታዊ አጀንዳዎችን ይቀርጻል አስቀድሞም ለም/ቤቱ አባላት እንዲታወቁ ያደርጋል፣
2. ም/ቤቱን በመወከል ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነቶችን ያደርጋል፣
3. የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ሰብሣቢዎች፣ ፀሃፊዎችና አባላት፣ የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ኃላፊ እንዲሁም ሌሎች በአፈ-ጉባኤው አቅራቢነት የሚሾሙ አካላትን አቅርቦ ያስመርጣል፣ ያሾማል::
4. የኮሚቴዎችን ሥራዎች ያስተባብራል፣
5. የምክር ቤቱን ጽ/ቤት ያደራጃል ጠቅላላ የአስተዳደር ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣
6. ምክር ቤቱ በአባሎች ላይ እንዲወሰድ የወሰነውን የዲስፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል::
7. ከሥልጣንና ተግባሩ ውስጥ በከፊል ለምክትል አፈ-ጉባኤው በጽሁፍ ሊሰጥ ይችላል፣
8. በም/ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

7. የምክትል አፈ-ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

ምክትል አፈ-ጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈ-ጉባኤውና ለምክር ቤቱ ሆኖ በህገ-መንግስቱና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

6. Powers and Duties of the Speaker

The Speaker, pursuant to the Constitution and this proclamation, shall have the following powers and duties:

1. Preside over the Council sessions and set agenda in collaboration with the concerned bodies and thereby notify same to members of the Council in advance;
2. Represent the Council in all its relations with third parties;
3. Cause election and appointment of chairpersons, secretaries and members of committees of the Council, present & get appointed by the Council Head of the Secretariat as well as other bodies;
4. Coordinate the activities of the committees;
5. Organize the secretariat of the Council and oversee general administrative activities;
6. Cause execution of disciplinary measures decided by the Council against its members;
7. May delegate part of his powers and duties to the Deputy Speaker in writing;
8. Undertake such other activities as may be assigned to him by the Council;

7. Powers and Duties of the Deputy Speaker

The Deputy Speaker being accountable to the Speaker and the Council shall have the following powers and duties pursuant to the Consitution and this proclamation:

1. አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ወይም አቋም ይዞ በምክር ቤቱ ውይይት ለመሳተፍ በሚፈልግበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል፣

2. በአፈ-ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

8. የምክር ቤቱ የስብሰባ አይነቶች፣ ምልዓተ-ጉባኤና የውሣኔ አሠጣጥ ሥርዓት

1. ምክር ቤቱ የሚከተሉት የስብሰባ አይቶች ይኖሩታል፦

   ሀ. መደበኛ ስብሰባ
   ለ. አስቸኳይ ስብሰባ

2. በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ /በአዋጅ ቁጥር 112/1997 ዓ.ም./ እንደተሻሻለ መሰረት ከማሻሽ በላይ የሚሆኑት የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ የምክር ቤቱ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። ውሣኔዎች በስብሰባው በተገኙ የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይተላለፋሉ።

9. ህግጋትና ደንቦችን የማውጣት ስነ-ስርዓት

1. ምክር ቤቱ ህግ የሚያወጣው አዳዲስ ህግጋትን በመደንገግ፣ ነባር ህግጋትን በማሻሻል ወይም በመሻርና የተለያዩ ውሣኔዎችን በማሳለፍ ይሆናል።

2. ህግ የማመንጨት ተግባር በዋነኝነት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት አካላት ይኸው ስልጣን አላቸው

   ሀ. አፈ-ጉባኤው፣
   ለ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣
   ሐ. የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች፣

1. Represent the Speaker in his absence or when he is unable to carry out his functions or when he wants to participate in the discussion of the Council siding to his own stand;

2. Undertake such other functions as may be especifically assigned to him by the Speaker.

8. Types of Meeting, Quorum and Decision Making Procedure of the Council

1. The Council shall have the following types of meetings:

   a) Regular Meeting;
   b) Extra ordinary Meeting.

2. Where more than half members of the Council present at the meeting shall constitute a quorum according to sub-Article 2 of Article 54 of the Constitution as amended by Proclamation No.112/2005; and decisions shall be passed by majority vote of council members present at the meeting.

9. Legislative Procedure

1. The Council shall enact law by promulgating of new statutes, amending or repealing old laws and passing various decisions.

2. As the principal draft law initiator shall be the Council of the Regional Government, the following bodies shall also have the power to initiate draft laws:

   a) The Speaker;
   b) The Regional Supreme court;
   c) Committees of the Council;

መ. የምክር ቤቱ አባላት፣

ሠ. ተጠሪነታቸው ለምክር ቤቱ የሆኑ ሌሎች መንግስታዊ አካላት፣

ረ. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የብሔረሰብ፣የወረዳ ወይም የከተማና የቀበሌ ምክር ቤቶች፣

ሰ. የብዙሃን ማህበራት።

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ቁጥሮች /ለ/ እና /ሠ/ የተጠቀሱት አካላት ህግን የሚያመነጩት በሕግ በተሰጣቸው ስልጣን ዙሪያ ይሆናል።

4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ስር የተደነገገው ቢኖርም ፋይናንስ ነክ ረቂቅ ህጋጉትን የማመንጨት ስልጣን የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ብቻ ነው።

5. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ቁጥር /መ/ መሰረት የሚቀርብ የህግ ረቂቅ በጽሁፍ ከተዘጋጀ በኋላ አቅራቢውን ጨምሮ ቢያንስ ሃያ የም/ቤቱ አባላት ፊርማ ተደግፎ ለአፈ-ጉባኤው መቅረብ አለበት።

6. ማናቸውም የህግ ረቂቅ በምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ በኩል ለምክር ቤቱ መቅረብ ይኖርበታል።

10. የመጀመሪያ ንባብ

1. አፈ-ጉባኤው በአጀንዳ የተያዘውን የህግ ረቂቅ ይዘቱን በአጭሩ ካቀረበ በኋላ አስተባባሪ ኮሚቴው በህጉ ዝርዝር ድንጋጌዎች ላይ እንዲወያይ ይደረጋል።

2. ውይይቱ እንደተጠናቀቀ የህግ ረቂቁ በአፈ-ጉባኤው አማካኝነት ቁጥር ተሰጠቶት ወደ ሚመለከተው ኮሚቴ ወይም ኮሚቴዎች ይመራል።

d) Members of the Council;

e) Other govrnment institutions accountable to the Council;

f) Nationality, Woreda or City or Kebele Councils in the Region;

g) Civic associations.

3. The bodies specified in sub-Article 2 (b) and (e) above, may initiate laws within their jurisdiction given to them by law.

4. Notwithstanding to the provision in sub-Article 2 and 3 above, only the Council of the Regional Government shall initiate financial draft laws.

5. A draft law to be presented in accordance with sub-Article 2(d) above shall be in writing and supported by at least 20 members of the Council and be submitted to the Speaker.

6. Any draft law shall be submitted to the Council through the Speaker.

10. First Reading

1. The Speaker shall breifly present a content of the draft law which is held as agenda, and later he/she causes the coordinating committee delibrate on the detail provisions of the draft law.

2. Upon winding-up of delibration on the draft law, it shall be numbered and referred to the pertinent committee(s) through the Speaker.

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ የሚወጣው ሕግ በአስቸኳይነቱ የሚታመንበት ካልሆነ በስተቀር ሕጉ የተመራለት ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን አጥንቶ የውሣኔ ሃሣቡን ለምክር ቤቱ ለማቅረብ ቢያንስ 15 የሥራ ቀናት ማግኘት ይኖርበታል።

11. ሁለተኛ ንባብ

1. አፈ-ጉባኤው ከመጀመሪያ ንባብ በኋላ ለቋሚ ኮሚቴ በተመራ የህግ ረቂቅ ላይ የተዘጋጀው የውሣኔ ሃሣብና አስተያየት በቋሚ ኮሚቴው አማካኝነት ለምክር ቤቱ እንዲነበብ ያደርጋል።

2. አፈ-ጉባኤው በቀረበው የውሣኔ ሃሣብ ላይ ዝርዝር ውይይት በምክር ቤቱ ይካሄድበት ዘንድ መድረክ ይከፍታል።

3. በህግ ረቂቁ ላይ የሚካሄደው ውይይት እንደተጠናቀቀ በሰነዱ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ምክር ቤቱ ያሳልፋል። ሊጠቃለል ካልቻለ ግን ለተጨማሪ ዕይታ ወደሚመለከተው ኮሚቴ ተመልሶ እንዲመራ ይደረጋል። ይመራል።

12. ሶስተኛ ንባብ

1. ዳግም ጉዳዩ የተመራለት ኮሚቴ የሚሻሻለውን አሻሽሎ የመጨረሻውን የውሣኔ ሃሣብ በማዘጋጀት ለም/ቤቱ በንባብ እንዲያሰማ ይደረጋል።

2. በቀረበው የመጨረሻ የውሣኔ ሃሳብ ላይ ም/ቤቱ በቂ ውይይት በማካሄድ ይወሰናል።

13. ሕጉ ስለሚፀድቅበት፣ ስለሚፈረምበትና ስለሚታተምበት ሁኔታ

1. አፈ-ጉባኤው የሕግ ረቂቁን ም/ቤቱ መክሮ የተስማማበት መሆኑን በመግለጽ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 3

3. The concerned standing committee to which the draft law is referred shall require at least 15 working days to examine the draft legislation and thereby submit its recommedation to the Council, unless the draft law to be issued in applying the provision of sub Article 2 of this Article is belived urgent for an immediate enactment.

11. Second Reading

1. Subsequent to the first reading, the Speaker shall cause the standing committee, to which the draft law has been referred, read out the draft proposals and comments it has forwarded on the draft law to the Council.

2. The Speaker shall open a platform for elaborate discussions on the submitted legislation draft proposals.

3. Upon winding-up of the delibration on the draft law, the Council shall pass final decision. If the delibration cannot be concluded, the draft law shall be referred to the pertinent committee for further investigation.

12. Third Reading

1. The committee to which the draft law is re-referred shall be caused to read out the amended version to the Council by preparing its final recommendations.

2. Subsequent to holding sufficient delibrations on the final draft proposals submitted, the Council shall make decisions thereto.

13. Ratifing, signing and publishing the law

1. The Speaker, inaccordance with the power vested in him under sub-Article 3/b/ of Article 60 of the Constitution,

ፊደል ተራ ቁጥር ለ ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይፈርምበት ዘንድ ለብሔራዊ ክልሉ ፕሬዚዳንት ይልከዋል::

2. ፕሬዚዳንቱም በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ይፈርማል:: በዚሁ የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልፈረመ ሕጉ በሥራ ላይ ይውላል::ሆኖም ሕጉ በክልሉ ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከመውጣቱ በፊት የቴክኒክ እርማት ማድረግ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ እርማቱን አፈ-ጉባኤው ያደርጋል::

3. የፀደቀው ህግ በአፈ-ጉባኤው አማካኝነት ቁጥር ተሰጥቶት በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ይታተማል::

4. ሕጉ ከመታተሙ በፊት ከቴክኒክ እርማት ባሻገር መሟላት ያለባት ክፍተት ሲገኝበት በሚመለከተው አካል አማካኝነት ክፍተቱን የሚያሟላ ሃሣብ ለምክር ቤቱ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ በዚያው ሕግ ላይ ተካቶ ይታተማል፣ ስለተካተተው ሃሣብም ከመታተሙ በፊት የክልሉ ፕሬዚዳንት እንዲያውቀው ይደረጋል::

14. መንግስታዊ አካላትን ስለመከታተልና ስለመቆጣጠር

1. ምክር ቤቱ የክልሉን መንግስታዊ አካላት የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ዋና አላማ:-

ሀ. የህዝብና የመንግስት ሃብትና ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን፣

ለ. ስራዎች ህግና ሥርዓትን መሠረት አድርገው እየተከናወኑ መሆኑን፣

ሐ. ፍትሃዊና ፈጣን የልማት አቅጣጫ መያዙን፣

መ. ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትንና መልካም አስተዳደር መስፈኑን፣

ሠ. የዜጐች መብት፣ ሠላምና ደህንነት መከበሩን፣

shall send the draft law to the president of the National Region for signitature with suggestion that the Council has discussed and ratified it.

2. The president shall sign a law submitted to him within fifteen days. If, however, the president does not sign the law within this time limit, the legilation shall come into force. The speaker of the Council may undertake technical correction, prior to its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

3. The approved law shall be numbered by the Speaker and thereby published in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

4. When non technical corrections are detected before publication of the law, a suggestion of corrections shall be submitted by the concerned body and be endorsed by the Council; the suggestion shall be included in the law and get published; the president of the National Region shall be informed about the suggestion incorporated in the law before it gets published.

14. Following up and Monitoring State Bodies

1. The main purpose of the Council to follow up and monitor the Regional State bodies shall be whether:

a) public and government resources and property are utilized properly;

b) activities are being carried out in accordance with rules and regulations;

c) there exists fair and rapid development direction;

d) democracy and good-governance are prevailing;

e) citizens rights, peace and security are maintained; and

ረ. በመንግስት አካላት መካከል የተቀናጀ አሠራር መኖሩን ማረጋገጥ ነው::

2. ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚከተሉት አካላት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል:-

ሀ. የክልሉ የመንግስታዊ አካላት፣

ለ. ለምክር ቤቱ ተጠሪ የሆኑ የራሱ የውስጥ አደረጃጀቶች::

15. ሪፖርት ስለማቅረብ

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በአመት 2 ጊዜ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል::

2. እያንዳንዱ የክልሉ መንግስታዊ አካል ለሚመለከተው የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ በተመደበለት ጊዜ ሪፖርት ማቅረብ አለበት::

3. ቋሚ ኮሚቴው የቀረበውን ሪፖርት አዳምጦ በሪፖርቱ ላይ ይፋዊ የሕዝብ ውይይት እንዲካሄድ ይደረጋል:: ጉዳዩ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎችና የመገናኛ ብዙሃን ወኪሎችም እንዲገኙ ያደርጋል:: አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥታዊ አካላት በሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ለም/ቤቱ ሪፖርት ሊያቀርቡ ይችላሉ::

4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ መሰረት የሚቀርበው ሪፖርት፣ በዋናነት ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና/ክንውን/ውጤት፣ አስተዳደራዊ ሂደቱና፣ የበጀት አፈፃፀሙን፣ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችን፣ አወንታዊ የሥራ ውጤቶችና የመሳሰሉትን ማካተት አለበት::

5. አስገዳጅ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር የሪፖርት አቅራቢው መስሪያ ቤት ኃላፊ ሪፖርቱን ያቀርባል::

f) there exixts a system of coordination among state bodies.

2. The Council, inaccordance with this proclamation, shall follow up and monitor the following bodies:

a) Organs of the Regional State;

b) Internal organizations of the council accountable to it.

15. Presentation of a report

1. Head of the Regional Government shall present to the council a report twice a year.

2. Any executive body of the Regional Government shall present a report to the concerned standing committee of the council within the set timetable.

3. The standing committee, having heard the report submitted to it, shall cause the undertaking of public discussions on it. It shall cause the concerned segment of the public and mass media agents to attend the discussion. The pertinent bodies of the Regional State, if found necessary, can present a report to the Council through the concerned standing committee.

4. The report to be submitted, pursuant to sub-Article 2 of this Article, shall mainly incorporate annual work plans and performance outcomes, administrative process, budget execution, major problems encountered, strong points of the work and the like

5. Unless circumstances otherwise compel, office heads shall present the report.

6. ሪፖርቱ በኃላፊው ተወካይ ሊቀርብ የሚችለው፣ ኃላፊው ሊቀርብ ያልቻለበትን ምክንያትና በተወካዩ የሚቀርብ መሆኑን ለአፈ-ጉባኤው አስቀድሞ በማሣወቅ ብቻ ይሆናል።

7. የምክቤቱ አባላት በአፈ-ጉባኤው በሚሰጣቸው ቅደም ተከተል መሰረት ለሪፖርት አቅራቢው ጥያቄና አስተያየት ያቀርባሉ።

8. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ መሰረት ለም/ቤቱ በተሰጡት መልሶች ዙሪያ ተጨማሪ ጥያቄዎችና አስተያየቶች እንዲቀርቡ ያደርጋል።

9. ሪፖርቱን አስመልክቶ የማጠቃለያ አስተያየት ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ም/ቤቱ የሚመለከተውን ቋሚ ኮሚቴ ተጨማሪ ማጣራትና ምርመራ አድርጎ ሪፖርት እንዲያቀርብለት ሊያዝ ይችላል።

10. ም/ቤቱ የቀረበውን ሪፖርት አዳምጦ መሰረታዊ ችግር አለበት ብሎ ያመነ እንደሆነ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

16. የዕለታዊ አጀንዳዎች አቀራረብ

1. ምክር ቤቱ የሚወያይባቸው አጀንዳዎች የሚመነጩት:-

ሀ. ከክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት፣

ለ. ከአፈ-ጉባኤው፣

ሐ. ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

መ. ከምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች፣

ሠ. ከምክር ቤት አባላት፣

ረ. ለምክር ቤቱ በቀጥታ ተጠሪ ከሆኑ ሌሎች አካላት፣

ሰ. ከፓርቲ ተጠሪዎች።

6. Where the report is presented by a representative of the official, the Head of the Office shall make an advance notification of this to the Speaker explaning the reasons for failing to show up presonally.

7. Members of the Council shall, according to the order given to them by the Speaker, raise questions and forward suggestions to the report prsenter.

8. Additional questions and comments shall be forwarded on the explanations and answers given in accordance with sub-Article 7 of this Article.

9. Concluding statments about the report shall be given; where necessary, the Council may order that a concerned standing committee make additional investigation and scrutining, and submit a report thereof.

10. Where the Council hears the report presented and believes that the report is with a basic problem, it shall take the necessary measure.

16. Setting of Agenda

1. The agendas on which the Council shall deliberate may emanate from:

a) The Council of the Regional Government;

b) The Speaker;

c) The Regional Superme Court;

d) Various Committees of the Council;

e) Members of the Council;

f) Other bodies that are directly accountable to the Council;

g) Party whips.

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር /ሀ/ ሥር በተጠቀሰው አማካኝነት የሚቀርብ ማናቸውም አጀንዳ ቅድሚያ ተሰጥቶት ውይይት ይደረግበታል::

2. Any agenda that emanates from the body stated under sub-Article 1/a/ above shall get priority for discussion.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚመነጩ አጀንዳዎች ለምክር ቤቱ የሚቀርቡት በአፈ-ጉባኤው በኩል ይሆናል::

3. Agendas that are initiated in accordance with sub-Article 1 of this Article shall be presented to the Council through the Speaker.

4. ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ማናቸውም የመወያያ አጀንዳ ጉባኤው ከመካሄዱ ከ1 ወር በፊት ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ መቅረብ ይኖርበታል::

4. Any agenda presented to the Council for delibration shall be submitted to the Speaker of the Council one month before the Council holds its meeting.

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም ምክር ቤቱ በሚሰበሰብበት ጊዜ ልንወያይበት ይገባል ተብሎ በአስቸኳይነቱ የታመነበት ማንኛውም ጉዳይ በምክር ቤቱ አባላት ከቀረበና ከግማሽ በላይ በሚሆኑት ድጋፍ ካገኘ በአጀንዳነት ተይዞ ውይይት ሊደረግበት ይችላል::

5. Notwithstanding to the provision provided in under sub-Article 4 of this Article, any issue that the Council belives to be urgent during its meeting may be held as agenda and discussed when it is presented by members of the Council and got the support of more than half of same.

6. በአጀንዳዎች አቀራረብ ቅደም ተከተልና ለውይይት የሚያስፈልገውን ጊዜ በተመለከተ የመንግስት ዋና ተጠሪ እና አፈ-ጉባኤው በጋራ በመመካከር ይወስናሉ::

6. The government chief whip and the Speaker shall decide together upon priority of agendas and time required for discussion.

7. የሌሎች የፓርቲ ዋና ተጠሪዎች እንዲያዙላቸው በሚፈልጓቸው አጀንዳዎችና ለጉዳዩ የሚያስፈልገውን የውይይት የጊዜ መጠን አስመልክቶ ከመንግስት ዋና ተጠሪ ጋር ይመካከራሉ::

7. Chief whips of other parties shall consult the government chief whip regarding their proposed agendas and time required to discuss the issue.

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በቀረቡ አጀንዳዎች ምክር ቤቱ በእያንዳንዱ ላይ ድምፅ ይሰጣል:: በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍም በአጀንዳነት ይያዛል::

8. The Council shall vote on each of the agendas presented pursuant to sub-Article 3 of this Article. The agenda supported by majority vote of the council shall be delibrated upon.

9. ምክር ቤቱ በአጀንዳነት ባፀደቃቸው ጉዳዮች ላይ በቂ ውይይት በማድረግ ውሣኔዎችን ያሣልፋል::

9. The Council shall pass decisions after adequately delibtating upon the approved agendas.

10. ምክር ቤቱ የተለየ አቅጣጫ ካላስቀመጠ በስተቀር በአንድ ጉባኤ ውድቅ የሆነ አጀንዳ በዚያው ዓመት ተመልሶ ለምክር ቤቱ አይቀርብም::

10. Unless stated by the Council other wise, an agenda rejected at one meeting of the Council shall not come again to the Council in same year.

ክፍል ሶስት

ስለምክር ቤት አባላት መብቶችና ግዴታዎች፣ የስነ-ምግባር ሁኔታ፣ ስለኮሚቴዎች ውስጣዊ አደረጃጀትና አሠራር

17. ስለምክር ቤቱ አባላት መብቶች፣ ግዴታና የሥነ-ምግባር ደረጃ

የምክር ቤቱ አባላት በሕገ-መንግስቱና በዚህ አዋጅ የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጓቸው ወይም የሚያስችሏቸው መብቶች ሁሉ ይኖሯቸዋል። በአንዳሩም የክልሉ ህዝብ የጣለባቸውን ኃላፊነቶችና የሥነ-ምግባር ግዴታዎች በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል። ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይደነገጋል።

18. ስለምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች

ምክር ቤቱ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/4/ና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት የኮሚቴ ዓይነቶች ይኖሩታል፡-

1. አስተባባሪ ኮሚቴ፣
2. ቋሚ ኮሚቴ፣
3. ንዑስ ኮሚቴ፣
4. ጊዜያዊ ኮሚቴ።

19. ስለአስተባባሪ ኮሚቴው አደረጃጀት፣ ሥልጣን፣ ተግባራትና አሰራር

1. አስተባባሪ ኮሚቴው፡-

ሀ. አፈ-ጉባኤውን፣ ምክትል አፈ-ጉባኤውን፣ የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሣቢዎችንና ፀሃፊዎችን ወይም ተወካዮቻቸውን በአባልነት የያዘ ነው፣

PART THREE
Rights, Obligations, Rules of Code of Conduct of Members of the Council and Internal Organization and Operation of the Committees

17. Rights, Obligations and Standard of Rules of Code of Conduct of the Members of the Council

Members of the Council shall have all rights that are necessary and enable them to exersise powers and duties entrusted to them by the Constitution and this proclamation. They shall properly discharge the responsibilities and rules of code of conduct laid upon them by people of the Region. Particulars shall be determined by a regulation to be issued pursuant to this proclamation.

18. Various Committees of the Council

The Council, in accordance with sub-Article 3/4/ of Article 49 of the Constitution and this proclamation, shall have the following types of committees:

1. Coordinating Committee;
2. Standing Committee;
3. Sub-Committee;
4. Ad-Hoc Committee.

19. Organization, Powers, Duties and operation of the Coordinating Committee

1. The Coordinating Committee shall:

a) Comprise the Speaker, the Deputy Speaker, chairpersons and secretaries or representatives of the latter of the standing committees as members;

ለ. የሚመራው በአፈ-ጉባኤው ሲሆን ውሣኔዎችን በአብላጫ ድምፅ ያሣልፋል፣ ከአባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፤

ሐ. ከአባላቱ መካከል የራሱን ፀሃፊ ይመርጣል::

2. የም/ቤቱ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ሀ. የኮሚቴዎችን የሥራ ዕቅድ ያስተባብራል፣ የምክር ቤቱን አጠቃላይ የሥራ ሂደት፣ ቅንጅትና ስኬታማነት ይከታተላል፤

ለ. በም/ቤቱ ውስጥ የሚከሰቱትን ዋና ዋና ችግሮችና አወንታዊ ጎኖች በሚመለከት በየወቅቱ ይገመግማል፣ አጠቃላይ የሥራ አቅጣጫ በመቀየስ ለሚመለከተው ኮሚቴ መመሪያ ይሰጣል፤

ሐ. አፈ-ጉባኤው በዚህ ኮሚቴ እንዲታዩ ያመነባቸው ጉዳዮችና እንዲሁም የቋሚ ኮሚቴ አባላት ተወያይተው በአስተባባሪ ኮሚቴው እንዲታዩ የሚወስኗቸውን አጀንዳዎች በተመለከተ ይወያያል፤

መ. አዳዲስ መንግስታዊ አካላት ሲደራጁ ወይም የነበሩት እንደ አዲስ ሲዋቀሩ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ይደረግ ዘንድ ጉዳዩን ከሥራ ጠባዩ ጋር ለሚዛመደው ቋሚ ኮሚቴ ይመራል፣ ይከታተላል::

3. ቋሚ ኮሚቴዎች እንዲከተሏቸው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 የተዘረዘሩትን አጠቃላይ የአሰራር ስልቶች አስተባባሪ ኮሚቴውም እንደ ስራ ባህሪው ተግባራዊ ሊያደርጋቸው ወይም ሊጠቀምባቸው ይችላል::

b) Be presided by the Speaker and pass decisions by majority vote; where more than half of its members present at the meeting, it shall constitute a quorum.

c) Elect its secretary from among its members.

2. The coordinating committee of the Council shall have the following powers and duties:

a) Coordinate the work plans of the committees, and supervise the general operational process, integration and effectiveness of the Council;

b) Evaluate timely the major problems and strong sides encountered within the Council; streamline general work plans and issue directives to the concerned committee thereof;

c) Hold discussion on issues that the Speaker believes to be seen by this committee and on agendas which members of standing committees discuss and decide to be looked by the coordinating committee.

d) Upon the establishment of new state bodies or when the old ones are structured in a new way, the coordinating committee shall refer the issue of same to the concerned committee for supervise and control having regard with the nature of their work; and follow up same thereof.

3. The coordinating committee, too, may implement or make use of the general operational systems of the standing committees specified in Article 29 of this proclamation, having regard the nature of its work.

20. የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት

1. ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፦

   ሀ. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

   ለ. የአቅም ግንባታና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

   ሐ. የበጀትና የመንግስት ሂሣብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

   መ. የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

   ሠ. የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ።

2. ቋሚ ኮሚቴዎቹ ተጠሪነታቸው ለም/ቤቱ ይሆናል።

3. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሣቢውንና ፀሃፊውን ጨምሮ በአፈ-ጉባኤው አቅራቢነት በክልሉ ም/ቤት የሚመረጡና ከ5 እስከ 9 የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል።

4. አንድ የም/ቤት አባል በአንድ ጊዜ ከአንድ ቋሚኮሚቴ በላይ አባል ሆኖ ሊሠራ አይችልም።

5. የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሣቢዎች ተጠሪነታቸው ለአፈ- ጉባኤውና ለየኮሚቴዎቻቸው ይሆናል።

21. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ፦

   ሀ. የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ምርትና ምርታማነትን እንዲያድግ፣ በምግብ እህል ራስን የመቻልና የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ዓላማችን ግብ እንዲመታ

20. Organization of the Standing Committee

1. The Council, pursuant to this proclamation, shall have the following standing committees:

   a) Economic Affairs standing Committee;

   b) Capacity Building and Social Affairs Standing Committee;

   c) Budgetary and Government Finance Affairs Standing Committee;

   d) Legal and Administrative Affairs Standing Committee; and

   e) Women's Affairs Standing Committee.

2. The standing committees shall be accountable to the Council.

3. Each standing committee shall have 5 to 9 members including the chairperson and the secretary who are elected by the Council upon recommendation by the Speaker.

4. A member of the Council shall not be a member of more than one standing committee at one time.

5. The chairpersons of the standing committees shall be accountable to the Speaker and their respective committees.

21. Economic Affairs Standing Committee

1. The main objective for establishing the Economic Affairs Standing committee is:

   a) To develop product and productivity of the agricultural economic sector; achieve the objective of ensuring food self sufficiency and food security;

እንዲሁም ግብርና-መር የሆነው የኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂያችን እንዲሣካ የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እቅዶች በተገቢው መንገድ መፈጸማቸውን መከታተልና መመርመር፤ እንዲሁም

ለ. የሃገሪቱ ንግድና እንዱስትሪ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የክልሉን የኢኮኖሚ ዕድገት በሚያፋጥን መልኩ ተግባራዊ መሆኑን፣ ንግድና፣ ኢንዱስትሪ እንደዚሁም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲስፋፉ የሚያበረታቱ ተግባራት በአግባቡ መከናወናቸውን፣ የኢንቨስትመንት ፖሊሲና ህግ በመስኩ ለሚሰማሩ ምቹ ሁኔታዎችን መፈጠራቸውን ማረጋግጥ ይሆናል።

2. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከዚህ በታች የተመለከቱትን መንግስታዊ መ/ቤቶች ይከታተላል፡-

ሀ. የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፣

ለ. የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ፣

ሐ. የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ፣

መ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥሮች ሀ እና ለ ስር ለተጠቀሱት ቢሮዎች ተጠሪ የሆኑ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች።

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ ሥር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማናቸውም ህጐች ተለይተው በተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ ረቂቅ ሕግ አዘጋጅቶ ለም/ቤቱ ያቀርባል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል።

4. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ስር የተሰጡትን ኃላፊነቶች በተሻለ አኳኋን ለመወጣት ራሱን በሚመለከት ሁለት ንዑሣን ኮሚቴዎች ከፋፍሎ ስራውን ያከናውናል።

follow up and examine policies, programmes and work plans issued for the attainment of the agriculture-led economy development strategy are implemented in a proper way.

b) To ensure that the country's Trade and Industry policy and strategy is implemented in manner to expedit the economic development of the Region; the proper undertakings of activities that encourage the promotion of trade, industry as well as small and micro enterprises; whether the investment policy and laws create conducive conditions for investors to involve in the sector.

2. The Economic Affairs standing Committee shall follow up Government Offices listed here below:

a) Agriculture and Rural Development Bureau;

b) Trade, Industry and Urban Development Bureau;

c) Water Resource Development Bureau,

d) Offices and organizations that are accountable to the bureaux cited under (a) and (b) herein above.

3. It shall prepare and submit a draft law to the Council concerning the powers and duties enumerated specifically by any laws to the bodies mentioned in sub-Article 2 of this Article; monitor, follow up and, where deemed necessary, examine same thereof.

4. The Economic Affairs Standing Committee, with a view to more effectively discharging its responsibilities specified under sub-Articles (2) and (3), shall undertake its activities by organizing itself into the following two sub-committees:

ሀ. የግብርናና ገጠር ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ፣

ለ. የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ።

5. የግብርናና ገጠር ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር ሀ ስር የተመለከተውን ቢሮና ለራሱ ተጠሪ የሆኑትን መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች አሰራር የሚከታተልና የሚመረምር ሲሆን የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ደግሞ በፊደል ተራ ቁጥር ለ ስር የተመለከተውን ቢሮና ለርሱ ተጠሪ የሆኑትን መንግስታዊ መስሪያቤቶች እንዲሁም በፊደል ተራ ቁጥር ሐ የተመለከተውን ቢሮ አሰራር የመከታተል ኃላፊነት ይኖርበታል።

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 የተደነገገው ቢኖርም የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች አስመልክቶ የሚዘጋጅ የህግ ረቂቅ ቢኖር ለአፈ-ጉባኤው የሚቀርበው በንዑሳን ኮሚቴዎች ሣይሆን በኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ይሆናል።

22. የአቅም ግንባታና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የአቅም ግንባታና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ፡-

ሀ. በክልሉ ውስጥ ፈጣን ልማትን ለማምጣትና በዴሞክራሲ የታነፀ ህብረተሰብን ለመፍጠር በብቃት፣ በጥራት፣ በታማኝነትና በቁርጠኝነት ሊሰራ የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል በአጭር ጊዜና በሰፊው ማፍራት፤

a) Agriculutral and Rural Develpment Affairs Sub-Committee;

b) Trade, Industry and Urban Development Affairs Sub-Committee.

5. Agricultural and Rural Development Affairs Sub-Committee shall follow up and examine the performance of the Bureau cited under sub-Article 1(a) of this Article and government offices that are accountable to it; the Trade, Industry and Urban Development Sub-Committee shall have the responsibility to follow up the performance of the Bureau cited under sub-Article 1(b) of this Article, government offices that are accountable to it as well as the Bureau indicated under sub-Article (1) (c) of same Article.

6. Nothwithstanding the provisions of sub-Articles (4) and (5) of this Article, any draft law prepared concerning the relevant offices shall be submitted to the Speaker through the Economic Affairs Standing Committee, but not by the Sub-Committees.

22. Capacity Building and Social Affairs Standing Committee

1. The main objective of establishing Capacity Building and Social Affairs Standing Committee is:

a) To develop wide range of human resource in a short period of time that is able to work efficiently, qualitatively, loyally and with commitment inorder to bring rapid development in the Region and create democratically shaped society;

ለ. የክልሉን አጠቃላይ የማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ የጤና ነክ አገልግሎት ማስፋፋትና የጤና ጠንቆችን ሚስወገድ፣

ሐ. የኤች አይ ቪ /ኤድስ/ ስርጭትን ለመግታት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን፣ የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎቶችን፣ ለጎዳና ተዳዳሪዎች፣ የአረጋዊያንና የአካል ጉዳተኞች ድጋፍና እንክብካቤ፣ የህፃናት ደህንነት ጥበቃ የሥራ አጥነትና ሌሎች የማህበራዊ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን አፈፃፀም እየተከታተለ፣ እያጠናና እየገመገመ፣ ህግ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ረቂቅ ህግ በማዘጋጀትና የሚመሩለትንም ሀሴች እያጠና አስተያየትና የውሣኔ ሃሣቦች ለምክር ቤቱ ማቅረብ ነው።

2. የአቅም ግንባታና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን መ/ቤቶች ይከታተላል፡-

ሀ. የአቅም ግንባታ ቢሮ፣

ለ. የህዝብ ተሣትፎና አደረጃጀት ጉዳዮች ቢሮ፣

ሐ. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣

መ. የወጣቶች፣ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ፣

ሠ. የጤና ጥበቃ ቢሮ፣

ረ. የማስታወቂያ ቢሮ፣

ሰ. የብዙሃን መገናኛ ድርጅት፣

ሸ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥር ሀ ና ረ ለተጠቀሱት ቢሮዎች ተጠሪ የሆኑ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች።

b) To promote policies and strategies of the general social development of the Region as well as health related services; and avoid health problems;

c) To follow up, study and evaluate the performances of activities undertaken to prevent the spread of HIV/AIDS; social welfare services; support and care for street children, old persons and the handicapped; people care for the well-beingness of children; unemployment, and other social affairs related issues; and thereto prepare draft laws for issues that require to do so, examine and submit to the Council proposals and suggestions on draft laws referred to it.

2. Capacity Building and Social Affairs Standing Committee shall follow up the following offices:

a) Capacity Building Bureau;

b) Public Participation and Organizational Affairs Bureau;

c) Labour and Social Affairs Bureau;

d) Youth, Culture and Sport Affairs Bureau;

e) Health Bureau;

f) Information Bureau;

g) Mass Media Agency;

h) Government offices and organizations that are accountable to the Bureau listed under (a) and (f) above.

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ የተዘረዘሩትን አካላት ብተመለከተ በማናቸውም ህጐች ተለይተው በተሰጧቸው ሥልጣንና ተግባራት ዙሪያ ረቂቅ ህግ አዘጋጅቶ ለም/ቤቱ ያቀርባል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል::

23. የበጀትና የመንግስት ሂሣብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የበጀትና የመንግስት ሂሣብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ የክልል መንግሥቱን ዓመታዊና ተጨማሪ በጀት፣ እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆነው ገንዘብና ንብረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በክልሉ ፖሊሲዎችና ህጐች መሰረት መከታተልና መቆጣጠር ነው::

2. የበጀትና የመንግስት ሂሣብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉትን መ/ቤቶች ይከታተላል:-

   ሀ. የዋና ኦዲተር መ/ቤት፣

   ለ. የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮ::

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ ስር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማናቸውም ህጐች ተለይተው በተሰጧቸው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ ረቂቅ ህግ አዘጋጅቶ ለም/ቤቱ ያቀርባል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል::

4. የክልሉን መንግስት አመታዊና ተጨማሪ የበጀት ረቂቅ አዋጆች በዝርዝር ይመረምራል፣ የውሣኔ ሃሣቡን በማከል ለም/ቤቱ ያቀርባል:

3. It shall prepare and submit to the Council draft laws concerning the powers and duties of bodies enumerated under sub-Article 2 of this Article; monitor, follow up and, when deemed necessary, examine same thereof.

23. Budgetary and Government Finance Affairs Standing Committee

1. The objective of establishing Budgerary and Government Finance Affairs Standing Committee is to follow up and monitor, pursuant to policies and laws of the Region, annual and suplementary budget of the Regional state; collection, maintenance and proper utilization of government finance and property.

2. Budgetary and Government Finance Affairs Standing Committee shall, in accordance with this proclamation, follow up the following offices:

   a) Office of the Auditor General;

   b) Finance and Economic Development Bureau.

3. It shall prepare and submit a draft law concerning the powers and duties specifcally entrusted to the bodies listed under sub-Article 2 0f this Article; monitor, follow up and, when deemed necessary, examine same thereof;

4. It shall examine the details of annual and supplementary budget draft proclamations of the Regional State.

24. የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ዋና አላማ:- የክልሉ መንግሥት የፍትህና አስተዳደራዊ ሥርዓቶች ህገ-መንግስቱን መሰረት በማድረግ መደራጀታቸውንና መፈፀማቸውን ለመከታተል፣ እንዲሁም በዚህ ዘርፍ ያለውን መሰረታዊ ችግር በማጥናት የሚታረምበትን አቅጣጫ መንደፍን በተመለከተ ሆኖ በተለይም:-

   ሀ. ህብረተሰቡ በህገ-መንግስቱ ያገኛቸውን መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በአግባቡ መተግበራቸውንና በሂደት ዙሪያ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች፣

   ለ. ህብረተሰቡ ከተፅዕኖ ነፃ በሆነ የዳኝነት ስርዓት በአግባቡ መገልገሉን፣

   ሐ. ህግ ነክ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና ስምምነቶች፣ መነደፋቸውንና መተግበራቸውን በተመለከተ ክትትልና ምርመራ ማድረግ ነው::

2. የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉትን መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ይከታተላል:-

   ሀ. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት፣

   ለ. ፍትህ ቢሮ ፣

   ሐ. የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ፣

   መ. የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን

   ሠ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥር ሐ ስር ለተመለከተው ቢሮ ተጠሪ የሆኑ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች::

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ ሥር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማናቸውም ህጐች ተለይተው በተሰጧቸው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ ረቂቅ ህግ አዘጋጅቶ ለም/ቤቱ ያቀርባል፣ይቆጣጠራል ፣ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል::

24. Legal and Administrative Affaris Standing Committee

1. The main objective of Legal and Administrative Affairs Standing Committee is to follow that justice and administrative systems of the Regional state are organized and implemented in accordance with the Constitution; and to study and thereby design a direction to rectify basic problems prevailing in this sector. In particular, it shall make follow up and examination concerning:

   a) The proper implementation of basic rights and freedoms which the public is guarnted by the Constitution and problems encountered thereto;

   b) The public is properly served by independent judical system; and

   c) Designing and implementation of legal related policies, strategeis, programmes and agreements.

2. Legal and Administrative Affairs Standing Committee shall, in accordance with this proclamation follow up the following government /state bodies:

   a) The Regional Superme Court;
   b) Justice Bureau;
   c) Administrative and Security Affaris Bureau
   d) Ethics and Anti-corruption Commission;
   e) Governemt offices that are accountable to the Bureau cited under Article 2(c).

3. It shall prepare and submit a draft law concerning the powers and duties given specifically to the bodies listed under sub-Article 2 of this Article; monitor, follow up, and, when deemed necessary, examine same thereof.

4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 /ሀ/ የተጠቀሰውን አካል በተመለከተ የህገ መንግስቱን አንቀጽ 64 መሰረት በማድረግና የዳኝነት ነፃነትን በማይጋፋ መልኩ ኮሚቴው ሥራውን ያካሂዳል።

5. ም/ቤቱ ወደ ማናቸውም ቋሚ ኮሚቴዎች የሚመራቸውን ረቂቅ ህጐች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የህግ ይዘታቸውን በተመለከተ ይመረምራል።

6. በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተውን የህግ ከለላ ለማንሣት እንዲሁም ሌሎች ከአባላት መብትና ግዴታዎች ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ሲመሩለት ወይም ሲቀርቡለት ሪፖርትና የውሣኔ ሃሣብ አዘጋጅቶ ያቀርባል።

7. በም/ቤቱ እንዲዋቀሩ የሚጠየቁ ማናቸውንም ተቋማት በተመለከተ አስተዳደራዊ መዋቅራቸው ከህገ-መንግስቱ ጋር በተጣጣመ መልኩ መደራጀታቸውን ይከታተላል፣

8. በምክር ቤቱ ተመክሮባቸው መጽደቅ ያለባቸው ማናቸውም ውሎችና ስምምነቶች ከህግ አኳያ ያላቸውን ተቀባይነት ይመረምራል።

25. የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ

1. የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ በህገ-መንግስቱ የተደነገጉትን የሴቶች መብቶች ማስከበርና በመብቶቻቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ መፍጠር ሲሆን በተለይም፡-

ሀ. ሴቶችን የሚጨቁኑ ህጐችን መመርመርና እንዲሻሻሉ ማድረግና አዳዲስ የህግ ሃሣቦችን ማመንጨት፣

4. Concerning the body indicated under sub-Article 2(a) of this Article, the committee shall carry out its activities in accordance with Article 64 of the Constitution and without prejudice to the judical independance.

5. It shall examine, when deemed necessary, the content of draft laws referred by the Council to any standing committees.

6. It shall prepare and submit to the Council a report and suggestion on suspending the legal immunity provided in sub-Article 5 of Article 48 of the Constitution as well as other questions referred & prestented to it in relation with members' rights and obligations.

7. It shall follow up that administrative structures of any bodies required to be structured by the Council are organized in conformity with the Constitution.

8. It shall beforehand examine, with respect to law, the acceptability of any contracts and agreements which are delibrated and endorsed by the Council.

25. Women's Affairs Standing Committee

1. The main objective of establishing Women's Affairs Standing Committee is to cause the respect for women's rights ensrhined in the Constitution and create a situtuation where they are beneficiaries of their rights; and especifically;

a) It shall examine and thereby cause amendament on laws deprive of women; initiate new legislation thereon;

ለ. አዋጆችና ዕቅዶች ሲወጡም ሆነ ሲፀድቁ የጾታ አድሎን ያስወገዱና ሥርዓተ ጾታን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ፣

b) When laws and work plans are issued or approved, it shall cause they should avoid gender inequality, and take geneder into account instead;

ሐ. በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ መስኮች እንዲሁም በመንግስትና በግል ተቋማት ሴቶች ከወንዶች እኩል ተወዳዳሪና ተሣታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል፣ በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃ /ትኩረት/ እንዲጠቀሙ ማድረግ፣

c) It shall cause affirmative action to be in use with a view to enabling women equally competitive and participative with men in political, economic and social sectors as well as in public and private institutions;

መ. ሴቶች ያሏትውን ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደርና የመቆጣጠር፣ የመጠቀም፣ የማስተላለፍና የመውረስ መብቶቻቸውን ማስከበርን፣

d) It shall cause respect of women's right to acquire, administer, control, utilize, transfer and inherit properties;

ሠ. ሴቶች ያላቸው በቅጥርና የደረጃ ዕድገት እንዲሁም የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ መብት እንዲከበር ማድረግ፣

e) It shall cause respect of women's right in employment and promotion as well as equal pay and transfer of pension;

ረ. ከጎጂ ባህል ተፅዕኖ ይላቀቁ ዘንድ ሴቶችን የሚጨቁኑና በአካላቸው ወይንም በአእምሯቸው ላይ ጉዳት የሚያደርሱትን ወግኖችና ልምዶች መከላከል፣

f) It shall protect compatriots and practices that deprive women and cause physical and psychological harm on them with a view to ditaching women from the influence of harmful practices;

ሰ. በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርትና የመረጃ አቅም የማግኘት መብታቸውን ማስከበር፣

g) It shall cause respect of women's right to have access to family planning education and information capacity inorder to protect harms occur on them due to pregnancy as well as delivery and care for their healthiness thereof;

ሸ. በጥያቄዎቻቸው ዙሪያ እንደ ፍላጎታቸውና እንደ ችግራቸው ዓይነት ተደራጅተው ሊታገሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል።

h) It shall facilitate conditions by which women are able to struggle being organized around their questions of interest and types of problems.

2. በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም. አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 5 ስር ለህዝብ ተሣትፎና አደረጃጀት ጉዳዮች ቢሮ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሰረት የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤትን አሰራር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል::

26. የቋሚ ኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር

የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከተሉት አጠቃላይ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል:-

1. በተመሩላቸው የህግ ረቂቆች ላይ የውሣኔ ሃሣብና አስተያየት እያዘጋጁ ለም/ቤቱ ያቀርባሉ፤

2. እንደየአግባቡ የተደለደሉላቸውን መንግስታዊ አካላት አሠራር ይከታተላሉ፣ ይቆጣጠራሉ፤

3. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ በተለያዩ መንገዶችና ሁኔታዎች የሚቀርቡላቸውን አቤቱታዎች እንደየአግባቡ ተቀብለው ያስተናግዳሉ::

4. በተቋቋሙበት ዓላማ ዙሪያ ጥናት ያካሂዳሉ ህጐች ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላሉ፤

5. ልዩ ልዩ ዓውደ ጥናቶችንና የውይይት መድረኮች ያዘጋጃሉ የልምድ ልውውጦችን ያደርጋሉ፤

6. ሥራቸውን በንዑሣን ኮሚቴዎች ከፋፍለው ሊያከናውኑ ይችላሉ፤

7 ሕግ የማውጣት ተግባርና የአስፈፃሚ አካላት ክትትል በሚደረግበት ወቅት ሂደቱ የጸታ አድልዎን ያስወገደና ሥርዓተ ጸታን ያገናዘበ መሆኑን ያረጋግጣሉ፤

2. Without prejudice to the powers vested in Public Participation and Orgnaization Affairs Bureau under sub-Article 5 of Article 13 of proclamation No.60/2001, Women's Affairs Standing Committee shall, pursuant to this proclamation, follow up and control the operation of Women's Affairs Office.

26. Powers and Duties of Standing Committees

The Council's Standing committees shall have the following common powers and duties:

1. Prepare and submit to the Council proposals and suggestions made on various draft laws referred to them;

2. Follow up and monitor the operation of government /state bodies assigned to them as deemed appropriate;

3. As particlulars determined by a directive, receive and entertain, as deemed appropriate, petitions presented to them in various ways and circumstances;

4. Undertake a study on objectives for which they are established, and follow up the implementation of laws, policies, stratgeies and work programmes;

5. Prepare various workshops and discussions and undertake experience sharing forums;

6. Undertake by dividing their activities into sub-committees;

7. When laws are made and executive bodies are oversighted, ensure that such processes avoid gender inequality and consider gender instead;

8. በም/ቤቱ ወይም በአፈ-ጉባኤው የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናሉ::

27. የቋሚ ኮሚቴዎች አመራሮች ሥልጣንና ተግባር

1. የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል:-

ሀ. ኮሚቴዎቹን በመወከል ከሌሎች ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ::

ለ. እንደየስራ ዘርፋቸው ለም/ቤቱ ሪፖርት ያቀርባሉ::

ሐ. ኮሚቴዎቻቸውን ይመራሉ፣ ያስተባብራሉ፣ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓቱንም ያስጠብቃሉ::

መ. ተጋባዥ እንግዶች እንዲገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ::

ሠ. በም/ቤቱ፣ በአፈ-ጉባኤውና በኮሚቴው የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናሉ::

2. የቋሚ ኮሚቴዎች ፀሃፊዎች በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል:-

ሀ. ሰብሣቢዎቹ በማይገኙበት ጊዜ ተክተው ይመራሉ::

ለ. የኮሚቴዎቹ ሰነዶችና ቃለ-ጉባኤዎች በአግባቡ መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣሉ::

ሐ. በኮሚቴዎችና በሰብሣቢዎቻቸው የሚሰጣቸውን ሌሎች ስራዎች ያከናውናሉ::

8. Carryout other activities assigned to them by the Council or the speaker.

27. Powers and Duties of Leaders of Standing Committees

1. The Chairpersons of Standing Committees shall have, pursuant to this proclamation, the following powers and duties:

a) Represent the committees in all their dealings with third parties.

b) Present a report to the Council pertaining to their work sector.

c) Direct and coordinate the committees; and observe the meeting procedure.

d) Facilitate conditions for the presence of invited guests.

e) Carryout other activities given to them by the Council, the Speaker and the standing committee.

2. The secretaries of standnig committees shall, in accordance with this proclamation, have the following powers and duties:

a) Represent the chairpersons in their absence.

b) Make sure that the committees' documents and minutes are properly kept and preserved; and

c) Carryout other activities assinged to them by the committees and their respective chairpersons.

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ስር የተገለፁት አመራሮች የሥራ እንቅስቃሴያቸውን በየኮሚቴዎቻቸው አባሎች ዕውቅና የመምራት ግዴታ አለባቸው::

28. የኮሚቴዎችን ሪፖርት ስለማዳመጥ

1. የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች አፈ-ጉባኤው በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በተሰጣቸው ተግባር ዙሪያ በአመራሮቻቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት ለም/ቤቱ ሪፖርት ያቀርባሉ::

2. ኮሚቴዎች የሚያቀርቡት ሪፖርት:-

   ሀ. ዓመታዊ አጠቃላይ የሥራ አፈፃፀማቸውንና

   ለ. በየጊዜው በም/ቤቱ የሚመሩላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ይሆናል::

3. የም/ቤቱ አባላት በቀረበው ሪፖርት ዙሪያ ውይይት ያደርጋሉ፣ አስተያየት ይሰጣሉ፣ እንደነገሩ ሁኔታ ውሣኔዎችን ሊያሣልፉ ይችላሉ::

29. የቋሚ ኮሚቴዎች አጠቃላይ አሰራር

የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከተሉት ዋና ዋና የአሠራር ስልቶችና ሥነ-ሥርዓቶች ይኖሯቸዋል፣

1. ከመጀመሪያ ንባብ በኋላ በአፈ-ጉባኤው የተመሩላቸውን ረቂቅ ህጐች እንደየሁኔታው:-

   ሀ. ማስታወቂያ በማውጣት፣

   ለ. አስረጂዎችንና ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸውን አካላት በመጋበዝ፣

3. The leaders specified in under sub-Article 1 and 2 of this Article shall have the obligation to undertake their activities with cognizance of respective committee members.

28. Hearing Report of Committees

1. The standing committees of the Council shall, according to the timetable set by the Speaker, present performance reports concerning their duties through their leaders or representatives.

2. The preformance report presented by the committees shall focus on;

   a) Annual and general work performance;

   b) Issues referred to them by the Council.

3. The Council members shall discuss on the report presented to them, give comments and, as the case may be, pass decisions thereon.

29. Working Procedure of Standing Committees

The C ouncil's S tanding c ommittees s hall have the following major working methods and procedures:

1. The Standing Committees submit a report and suggestion to the Council ondraft laws referred to them by the Speaker, subsequent to the first reading, as the case may be, by:

   a) Putting up notices;

   b) Inviting resource persons and bodies directly pertinent to the issue; and

ሐ. የህዝብ አስተያየት መስጫ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ ሪፖርትና የውሣኔ ሃሣብ ለም/ቤቱ ያቀርባሉ።

2. ቋሚ ኮሚቴዎች የመመርመርና የመከታተል ሥራዎችን የሚያከናውኑት በሚከተሉት ስልቶች በመጠቀም ይሆናል፦

ሀ. ከሚከታተሏቸው መ/ቤቶች እቅዶችንና የክንውን ሪፖርቶችን በመቀበል፣

ለ. ስብሰባዎችንና ኮንፈረንሶችን በማሣተፍ፣

ሐ. የሚመለከታቸውን አካላት ጠርተው በማነጋገር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙትም መግለጫ እንዲሰጡ በማድረግ፣

መ. ለሥራው አጋዥ የሆኑ የተለያየ ጉብኝት በማድረግ፣

ሠ. ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚደርሷቸውን ጥቆማዎችና አቤቱታዎች መነሻ በማድረግ፣

ረ. ከሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች ወይም አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር፣

ሰ. ሪፖርት በማዘጋጀት ወይም መግለጫዎችን በመስጠት፣

ሸ. በዓመታዊ ዕቅድ በመምራት እና አጠቃላይ አሠራራቸውን በመገምገም።

30. የቋሚ ኮሚቴዎች የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

1. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የቋሚ ኮሚቴው አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

c) Facilitating platforms for public opinions.

2. The standing committees shall undertake their investigation and follow up acitvities through the use of the following methods:

a) by acquiring annual work plans and performance reports from offices which they follow up;

b) by participating in meeting and conferences;

c) by summoning and consulting concerned bodies and causing them to give statements when deemed necessary;

d) by making various supportive field visits to its activities;

e) by embarking upon information and compliants from various sections of the society.

f) by creating integration with other standing committees or bodies;

g) by preparing report or making statements; and

h) by causing them guided by their annual work plan and evaluating their over all operation.

30. Meeting procedure of Standing Committees

1. The presence of more than half of standing committee members in a meeting shall constitute a quorum.

2. የቋሚ ኮሚቴው ውሣኔዎች በአብላጫ ድምፅ ይተላለፋሉ፣ ሆኖም ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ በሰብሣቢው የተደገፈው ሃሣብ የኮሚቴው ውሣኔ ሆኖ ያልፋል።

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው እንዲሁም የኮሚቴዎች የስብሰባ አካሄድና የውሣኔ አሰጣጥ ሁኔታ የምክር ቤቱን የአሰራር ስነ-ስርዓት የሚከተል ሆኖ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

31. የቋሚ ኮሚቴዎች አባላት መብቶችና ግዴታዎች

1. የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች አባላት ከእለት ተእለት የኮሚቴ ሥራዎቻቸው ጋር የተያያዙ መብቶች ይኖሯቸዋል።

2. የቋሚ ኮሚቴዎች አባላት የሚከተሉት ዋና ዋና ግዴታዎች ይኖሩባቸዋል፦

ሀ. በበቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም የኮሚቴው ስብሰባዎች የመገኘት፣

ለ. የተመደቡላቸውን ሥራዎች በአግባቡ የመከታተልና የማከናወን፣

ሐ. በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር የሚደረጉ ጥናቶች፣ ስብሰባዎችና ሌሎች የመስክ ሥራዎች በሚወክል አባል በኩል ስለሁኔታው የተጠናከረ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል የማቅረብ።

2. The decision of a standing committee shall be passed by a majority vote; where the vote draws in a tie, the motion supported by the chairperson shall be passed as decision of the committee.

3. The provisions indicated under sub-Articles 1 and 2 herein above as well as the conduct of meeting and decisions rendering conditions shall be in accordance with the working procedure of the Council, and the detail be determined by a regulation thereof.

31. Rights and Obligations of Members of the Standing Committees

1. Members of the standing committees of the Council shall have rights in relation to their day-to-day works of the committees.

2. Members of the standing committees shall have the major obligations herein below:

a) Unless sufficient reason otherwise is present, he/she shall attened any meetings of the committee;

b) They shall properly follow up and undertake activities assigned to them;

c) They shall present a consolidated report through their delegated member regarding studies, meetings and other field works undertaken within the country or abroad.

3. እያንዳንዱን የኮሚቴ አባል በተናጠልም ሆነ በጋራ ለሚያከናውነው ተግባር ኃላፊነት አለበት፣ ግዴታውን የማይወጣ ማንኛውም የኮሚቴ አባል በኮሚቴው አብላጫ ድምፅ ተገምግሞ ለም/ቤቱ ሪፖርት ይቀርብበታል። የእርምት እርምጃ ይወሰድበታል።

32. የንዑሣን ኮሚቴዎች አደረጃጀት፣ ሥልጣን፣ ተግባርና አሠራር

1. ንዑስ ኮሚቴ ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት ሲባል የራሱን አባላት አመቺ በሆነ መልክ በመከፋፈል የሚያደራጀው አካል ነው።

2. በቋሚ ኮሚቴው አባላት የሚመረጡ ማናቸውም ንዑስ ኮሚቴዎች የየራሣቸው ሰብሣቢና ፀኃፊ ይኖሯቸዋል።

3. ንዑሣን ኮሚቴዎች በቋሚ ኮሚቴው ዓመታዊ የሥራ እቅድ ላይ በመመርኮዝ የየራሣቸው የሥራ እቅድ ያዘጋጃሉ፣ ይፈጽማሉ፣ ለቋሚ ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባሉ፣ በቋሚ ኮሚቴው የሚሰጣቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናሉ።

33. የጊዜያዊ ኮሚቴ አደረጃጀት፣ ሥልጣን፣ ተግባርና አሠራር

1. ም/ቤቱ በቋሚ ኮሚቴዎችና በአስተባባሪ ኮሚቴው በቀጥታ ሊከናወኑ የማይችሉ አስቸኳይና አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸው ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል።

3. Each member of the committee shall be responsibile for the duty he/she undertakes independently or jointly; where any member of the committee fails to discharge his/her obligation shall be evalutaed by majority vote of the committee and the report submitted to the Council; corrective measures shall be taken against him/her thereof.

32. Organization, Power, Duty and Operation of sub-Committees

1. A sub-committee is a body to be organized by any standing c ommittee through the assignment of its members in a suitable form with a view to efficiently discharging its responsibilities.

2. Any sub-committees chosen by the members of the standing committee shall have their own chairperson and secretary.

3. Sub-committees shall prepare their own work plan based on the annual work plan of the standing committee; and implement same; submit a report to the satnding committee thereon; carry out other acivities assigned to them by the standing committees.

33. Organization, Power, Duty and Operation of Ad-hoc Committee

1. The Council may establish Ad-hoc committees where it belives it is confronted with urgent and important conditions that cannot be undertaken by the standing committees and the coordinating committee.

2. የጊዜያዊ ኮሚቴ ሥልጣን በሚከሰተው አስቸኳይና አስፈላጊ ጉዳይ ዙሪያ ሆኖ ተልዕኮውን ለማከናወን አጠቃላይ የአሰራር አቅጣጫ በም/ቤቱ የሚሰጠው ይሆናል::

3. የጊዜያዊ ኮሚቴ አባላት ብዛት እንደሁኔታው በም/ቤቱ የሚወሰን ሆኖ፣ ኮሚቴውን የሚመሩ ሰብሣቢና ፀኃፊ ም/ቤቱ ይመድቡለታል::

4. ማናቸውም ጊዜያዊ ኮሚቴ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ ሥራውን አጠናቆ ለም/ቤቱ ሪፖርት ካቀረበ በኋላ የሚከስም ይሆናል::

34. የፓርቲ ተጠሪዎች አጠቃላይ አደረጃጀት

1. በምክር ቤቱ ውስጥ መቀመጫ ያላቸው የፓርቲ ተጠሪዎች በሚከተለው ሁኔታ ተደራጅተዋል:-

   ሀ. የመንግስት 1 ዋና ተጠሪ እና ከ 3 የማይበልጡ ረዳት ተጠሪዎች፣

   ለ. የዋናው ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ 1 ዋና ተጠሪ እና 2 ረዳት ተጠሪዎች፣

   ሐ. የሁለተኛው ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ 1 ዋና እና 1 ረዳት ተጠሪዎች፣

   መ ሌሎች በምክር ቤቱ መቀመጫ ያላቸው ፓርቲዎች አንድ አንድ ተጠሪዎች ይኖሯቸዋል::

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር /ሀ/ ሥር የተጠቀሰው የመንግስት ዋና ተጠሪ የሚወከለው በርዕሰ መስተዳደሩ ይሆናል::

2. The powers of the Ad-hoc committee shall depend on urgent and important situtations to be happening, and the Council shall give it general operational direction to undertake its mission.

3. The Council shall, as the case may be, determine the number of members of the Ad-hoc committee. The chairperson as well as the secretary to lead the committee shall be assinged to it by the Council.

4. Any Ad-hoc committee shall expire after completing its work and submitting a report to the Council pertainig to the power and duty given to it.

34 . Organization of Party Whips

1. Party whips that have seats in the Council are hereby organized as follows:

   a) One chief government whip and assistant whips exceeding not three;

   b) One chief whip and two assistant whips of the principal opposition political party;

   c) One chief and one assistant whips of the second opposition political party;

   d) Other parties that have seats in the Council shall have one whip each.

2. The Government chief whip stated under sub-Article 1 (a) herein above shall be appointed by Head of the

ተጠሪነቱም በቀጥታ ለእርሱ ነው። የመንግስት ረዳት ተጠሪዎችን ርዕሰ መስተዳድሩ ከዋናው ተጠሪ ጋር በመመካከር ይሰይማል።

3. በምክር ቤቱ ውስጥ ያሉ የተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪዎች የሚወከሉት በፓርቲ መሪዎቻቸው ወይም በምክር ቤቱ ውስጥ ባሉ አባሎቻቸው አማካኝነት ይሆናል። ተጠሪነታቸውም ለወከላቸው ፓርቲ ይሆናል።

35. የፓርቲ ተጠሪዎች ስልጣንና ተግባር

1. የመንግስት ዋና ተጠሪ የሚከተሉት አጠቃላይ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ. አባሎቻቸው መንግስት በምክር ቤቱ ውስጥ የሚኖሩትን የጉባኤ አጀንዳዎች አስቀድመው እንዲያውቁ፣ በስብሰባዎች እንዲገኙ፣ ለፓርቲያቸው ድምፅ እንዲሰጡና በማናቸውም መልኩ ብቁና ዝግጁ ሆነው እንዲገኙ ያደርጋል፤

ለ. በፓርቲው አመራር እና በምክር ቤቱ ባሉ አባላቱ መካከል የተቀናጀ ግንኙነት ይፈጥራሉ፤

ሐ. ፓርቲውን በመወከል በምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎችም ሆነ በሌሎች ፓርቲውን በሚመለከቱ ተልእኮዎች የሚሳተፉ አባሎችን ዝርዝር ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባሉ። በምክር ቤቱ ውስጥ በቋሚነት የተጓደሉ የፓርቲው አባላት በህግ መሰረት እንዲሟሉ ያደርጋል፤

መ. በምክር ቤቱ ሥራዎች እና አሠራሮች ዙሪያ መንግስትን ያማክራል፣ ከአፈ-ጉባኤው ጋር በመመካከር የአጀንዳዎችን ቅደም ተከተል ይለያል፣ ለውይይት የሚያስፈልገውን ጊዜም እንዲመደብ ያደርጋሉ።

Government, and be directly accountable to him. The later shall, in consultation with the chief whip, appoint assistant whips.

3. Opposition party whips in the Council shall be appointed by their party leaders or by their members in the Council; and they shall be accountable to the party that represent them.

35. Powers and Duties of Party Whips

1. The Government chief whip shall have the following powers and duties:

a) Inform his members about agendas of the Council before hand, and cause his party members present on meetings and vote for their party; and be prepared and efficeint for their work under any circumstances;

b) Create an integrated reltionship between leadership of his party and respective party members in the Council;

c) Submit, to the concerned bodies, a list of his members who participate in various committees of the Council as well as in other missions concerned with the party by representing the party; cause his party members permanently resigned from the Council be fulfiled pursuant to law;

d) Consult the government regarding activities and operations of the Council; arrange, in consultation with the Speaker, the sequence of the agendas and cause the allocation of time required for discussion.

ሠ. በምክር ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ የፓርቲ ተጠሪዎች ጋር እንደአስፈላጊነቱ ምክክር ያደርጋል፣ እርሱ በማይኖርበት ጊዜ ከረዳቶቹ ውስጥ ላንዱ ውክልና ይሰጣል፤

2. የመንግስት ረዳት ተጠሪዎች ከዋናው ተጠሪ ተለይቶ የሚሰጣቸውን ተግባራት ያከናውናሉ::

3. በምክር ቤቱ ውስጥ መቀመጫ ያላቸው ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ተጠሪዎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል:-

ሀ. አባሎቻቸው ስለምክር ቤቱ አጀንዳዎች አስቀድመው እንዲያውቁ፣ በስብሰባዎች እንዲገኙ፣ ለፓርቲያቸው ድምፅ እንዲሰጡና በአጠቃላይ ብቁና ዝግጁ ሆነው እንዲገኙ ያደርጋሉ፤

ለ. በፓርቲያቸው አመራርና በምክር ቤቱ ባሉ አባሎቻቸው መካከል የተቀናጀ ግንኙነት ይፈጥራሉ፤

ሐ. ፓርቲያቸውን በመወከል በምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎችም ሆነ በሌሎች ፓርቲያቸውን በሚመለከቱ ተልእኮዎች የሚሣተፉ አባሎቻቸውን ዝርዝር ለሚመለከተው አካል ያቀርባሉ፤

መ. በምክር ቤቱ ውስጥ በቋሚነት የተገደሉ የፓርቲያቸው አባላት በህግ መሰረት እንዲሟሉ ያደርጋሉ:: በምክር ቤቱ ሥራዎችና አሰራሮች ዙሪያ ፓርቲዎቻቸውን ያማክራሉ፤

ሠ. በሚያመነጯቸው አጀንዳዎች እና የሕግ ረቂቆች ዙሪያ ከመንግስት ዋና ተጠሪ ጋር ምክክር ያደርጋሉ:: የፓርቲው ዋና ተጠሪ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ የሚሰራው ሰው ከረዳት ተጠሪዎች መካከል ይወከላል::

e) Consult, as deemed necessary, with party whips in the Council; assign an a ssistant t hat w ould a ct on his behalf upon his absence;

2. Government assistnt whips shall carry out functions specifically assgned to them by the chief whip.

3. Other Political Party Whips having seats in the Council shall have the following powers and duties:

a) Inform their members about agendas of the Council before hand; cause their party members to be present on meetings and vote for their party; and cause them to be generally efficient and prepared for their work;

b) Create an integrated relationship between leadership of their parties and their members in the Council;

c) Submit, to the concerned body, a list of their members who participate in various committees of the Council as well as in other missions concerned with their parties by representing their parties;

d) Cause their party members permanently resigned from the Council be fulfiled pursuant to law; consult their respective party regarding activities and operations of the Council;

e) Consult with the government chief whip regarding agendas and draft laws which they initiate; and the chief whip of the party shall assign a person from among assistant whips that would act on his behalf upon his absence;

4. የዋናና ሁለተኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፖርቲ ሪዳት ተጠሪዎች በዋና ተጠሪያቸው ተለይቶ የሚሰጣቸውን ተግባራት ያከናውናሉ።

4. Assistant whips of the principal and second opposition political parties shall carry out duties especifically assigned to them by their principal whip.

36. ስለ ምክር ቤቱ የሥነ ሥርዓት አስከባሪ ሃይል

1. ምክር ቤቱ በጉባኤ ወቅት ስራውን በአግባቡና ሥርዓት ባለው መንገድ መወጣት ይቻለው ዘንድ ከክልሉ አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ እንደ አስፈላጊነቱ የሚመደብለት የሥነ ሥርዓት አስከባሪ ሃይል ይኖረዋል።

2. የሥነ ሥርዓት አስከባሪ ሃይሉ በጉባኤ ወቅት በምክር ቤቱ የስብሰባ አዳራሽና ቅጥር ግቢ ውስጥ ሀግና ሥርዓትን ይጠብቃል፣ ያስከብራል።

3. ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ መሰረት አድርጎ ወደፊት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

36. Security Maintaing Force of the Council

1. The Council shall have a security maintaining force assigned by the Regional Administration and Security Affaris Bureau, as deemed necessary, with a view to undertaking its activities appropriately and in a desciplinary manner during meetings.

2. The security maintaining force shall keep and maintain peace and security in the assembly hall and premises of the Council during meetings.

3. Particulars shall be determined by a regulation to be issued pursuant to this proclamation.

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

Part Four

Miscellaneous provisions

37. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሠራር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 63/1994 ዓ.ም. ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል።

37. Repealed and Inapplicable Laws

1. Legislative Procedure, Committee Organization and Operation of the Amhara National Regional Council Defining Proclamation No.63/2002 is hereby repealed and replaced by this proclamation.

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

38. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ የሰፈሩትን ድንጋጌዎች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል::

2. አፈ ጉባኤው ይህንን አዋጅና አዋጁን ተከትሎ ወደፊት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል::

39. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
ጥር 10 ቀን 1998 ዓ.ም.

አያሌው ጎበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

2. Any law, regulation, directive or customary practices in consistent with this proclamation shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

38. Power to Issue Regulation and Directive.

1. The Council may issue regulations necessary for full implementation of provisions provided in this proclamation.

2. The Speaker may issue directives necessary for the implementation of this proclamation and the regulation to be issued subsequent to the proclamation.

39. Effective Date

This Proclamation shall come into force commencing the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 18th Day of January, 2006

Ayalew Gobezie
President of the Amhara
National Regional State